የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሣኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.18
ADDIS ABABA 6th March, 2024

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲/፪ሺ፲፮

የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች የደህንነት ማረጋገጫና ቁጥጥር አዋጅ……………………………..ገጽ ፲፭ሺ፫፻፲፭

## Content

Proclamation No. 1310/2023

Information Technology Products Security Clearance and Control Proclamation ……..... ……………………………................... Page 15315

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲/፪ሺ፲፮

### የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች የደህንነት ማረጋገጫና ቁጥጥር አዋጅ

ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የሀገርን ምርታማነትና ውጤታማነት በማሳደግ እና የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ በማሻሻል ለሀገር ዘላቂ ልማት የሚያበረክተውን አዎንታዊ አስተዋፅዖ ደህንነቱ በተረጋገጠ መልኩ ማስቀጠል ተገቢ በመሆኑ፤

ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች ዕድገትና መራቀቅ ጋር ተያይዘው የሚመጡ አሉታዊ ተፅዕኖች በሀገራዊ የኢንፎርሜሽን ሀብቶች ደህንነት እንዲሁም በዜጎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጥቃቶችን አስቀድሞ መከላከልና መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኢንፎርሜሽን ደህንነት ስጋት የሚፈጥሩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶችን ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገቡ፣ ከሀገር በሚያስወጡ፣ እንዲሁም በተለያየ መልኩ ጥቅም ላይ በሚያውሉ ተዋንያን ላይ ግልፅ ኃላፊነት መደንገግ በማስፈለጉ፤

ወደሀገር ውስጥ እንዳይገቡ የሚከለከሉ እና በገደብ የሚገቡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶችን ለመለየት፣ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን ለመወሰን እና በምርቶቹ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ግልፅ፣ ወጥ እና ፍትሃዊ አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## PROCLAMATION NO. 1310/2023

### INFORMATION TECHNOLOGY PRODUCTS SECURITY CLEARANCE AND CONTROL PROCLAMATION

**WHEREAS**, it is imperative to maintain information technology's positive contribution to the nation's sustainable growth by raising national production and efficiency and enhancing residents' quality of life in a secure manner;

**WHEREAS**, it is necessary to prevent and minimize potential attacks on national information resources and citizens, resulting from negative impacts associated with the advancement and sophistication of technology products;

**WHEREAS**, it is necessary to impose a clear responsibility on actors who import, export, and use information technology products that pose a threat to information security;

**WHEREAS,** it is necessary to establish a transparent, consistent, and equitable system capable of identifying prohibited and restricted information technology products, determining security clearance procedures, and monitoring and controlling the products;

የተከለከሉ እና ገደብ የተጣለባቸው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶችን ከሕግ ውጭ ወይም አግባብነት ያለውን የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይዙ ቁጥጥር በሚደረግባቸው ተግባራት በተሰማራ ሰው ላይ ተገቢ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሕግ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል። ፲፭ሺ፫፻፲፭

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች የደህንነት ማረጋገጫና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርት" ከዚህ በኋላ "ምርት" እየተባለ የሚጠራው ማለት የኤሌክትሮኒክ ዳታዎችንና ሲግናሎችን ለማነፍነፍ፣ ለማስተጓጎል፣ ለመጥለፍ፣ ለመደምሰስ፣ ለማሳሳት፣ ለማወክ፣ ለመስረቅ እና ተዓማኒነት ለማሳጣት የሚያስችል እና በኢንፎርሜሽን ደህንነት ላይ ስጋት ሊፈጥር የሚችል የቴክኖሎጂ ቁስ፣ ንድፍ፣ ስልተ-ቀመር፣ ዘዴ፣ አገልግሎት ወይም መተግበሪያን ያጠቃልላል፤

፪/ "ኤሌክትሮኒክ ዳታ" ማለት በማንኛውም ዓይነት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርት የሚመረት፣ የሚቀመጥ፣ የሚሰራጭ፣ የሚተነተን ወይም ጥቅም ላይ የሚውል ኢንፎርሜሽን፣ ዳታ ወይም ፕሮግራም ነው፤

፫/ "የኢንፎርሜሽን ደህንነት ስጋት" ማለት ኢንፎርሜሽን በሚሰበሰብበት፣ በሚተነተንበት፣ በሚከማችበት፣ በሚሰራጭበት ወይም ጥቅም ላይ በሚውልበት ወቅት ተዓማኒነቱን፣ ሚስጥራዊነቱንና ተደራሽነቱን ሊያሳጡ የሚችሉ ስጋቶች ናቸው፤

**WHEREAS,** it is important to pass legislation for the imposition of suitable corrective action against persons who illegally or without proper security clearance utilize prohibited and restricted information technology products that pose an information security risk;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "Information Technology Products Security Clearance and Control Proclamation No. 1310 /2023".

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise in this Proclamation:

1/ **"Information Technology Product" (herein after refered to as "Product")** means any technology device, design, algorithm, method, service, or application that can infiltrate, disrupt, intercept, destroy, mislead, distort, steal, and falsify electronic data or signals;

2/ **"Electronic Data"** means information, data, or program that is produced, stored, disseminated, analyzed, or used in any type of information technology product;

3/ **"Information Security risks"** means attacks that may compromise the confidentiality, integrity, and availability of information when it is collected, analyzed, stored, disseminated, or used;

፬/ “ክልከላ የተደረገበት ምርት” ማለት በሀገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ላይ ሊያደርስ ከሚችለው አሉታዊ ተፅዕኖ አንፃር በዚህ አዋጅ መሠረት ወደ ሀገር እንዳይገባ፣ ከሀገር እንዳይወጣ ወይም ጥቅም ላይ እንዳይውል ሙሉ ክልከላ የተጣለበት የቴክኖሎጂ ምርት ነው፤

፭/ “ገደብ የተደረገበት ምርት” ማለት በኢንፎርሜሽን ደህንነት ላይ ሊያደርስ ከሚችለው አሉታዊ ተፅዕኖ አንፃር በዚህ አዋጅ መሠረት አግባብነት ባለው የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ብቻ ወደ ሀገር እንዲገባ፣ ከሀገር እንዲወጣ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውል ገደብ የተደረገበት የቴክኖሎጂ ምርት ነው፤

፮/ “ቁጥጥር የሚደረግበት ተግባር” ማለት ክልከላ ወይም ገደብ የተደረገባቸውን ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት፣ ከሀገር የማስወጣት፣ የማምረት፣ የመገጣጠም፣ የመፍጠር፣ የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የመያዝ፣ የማዘዋወር፣ የማስተዋወቅ፣ ጥቅም ላይ የማዋል እና ጥቅም ላይ እንዲውል የማመቻቸት ተግባራትን መቆጣጠርን ያጠቃልላል፤

፯/ “የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ” ማለት ይህን አዋጅ መሠረት በማድረግ የተለዩ ገደብ የተጣለባቸውን ምርቶች ወደ ሀገር ለማስገባትና ለማስወጣት ወይም ጥቅም ላይ ለማዋል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

፰/ “የሚመለከታቸው አካላት” ማለት በማቋቋሚያ ሕጋቸው የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎች ምርቶች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ቁጥጥር እንዲያደርጉ ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግስት ተቋማት ናቸው፤

፱/ “መውረስ” ማለት የተከለከሉ ወይም የፀና ፈቃድ የሌላቸው ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ምርቶች ከአዋጁ ውጪ በማንኛውም አካል ተይዘው ሲገኙ ውርስ ሆነው በጉምሩክ ሕግ መሠረት ለመንግሥት ገቢ የሚደረጉበት ሥርዓት ነው፤

፲/ “አስተዳደር” ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ነው፤

4/ **“Prohibited Product”** means a technology product due to its potential risk to national information security, prohibited from entering or leaving the country, or from being used in the country under this Proclamation;

5/ **“Restricted Product”** means a technology product due to its potential risk to national information security, restricted from entering or leaving the country, or from being used without having an appropriate security clearance permit under this Proclamation;

6/ **“Regulated Activity”** means regulating activities such as importing, exporting, manufacturing, assembling, creating, selling, exchanging, possessing, trafficking, promoting, utilizing, and facilitating the use of prohibited or restricted products;

7/ **“Security Clearance Permit”** means a permit issued to import, export, or use restricted products that are identified based on this Proclamation for a specific purpose;

8/ **“Relevant Entities”** means government institutions that are directly or indirectly responsible for information communication technology control through their establishing law;

9/ **"Forfeiture"** is a system in which prohibited or unlicensed, potentially threatening products are forfeited by the government as per customs regulations when they are acquired by any person in contravention of this proclamation;

10/ **“Administration”** means Information Network Security Administration;

፲፩/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፪/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

### ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ ምርቶችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣ ከሀገር በማስወጣት፣ በማምረት፣ በመፍጠር፣ በመሸጥ፣ በመለወጥ፣ በመያዝ፣ በማዘዋወር፣በማስተዋወቅ፣ ጥቅም ላይ በማዋል ወይም ጥቅም ላይ እንዲውል የማመቻቸት ተግባር ላይ በተሰማራ ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ቢኖርም ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት፣ በፌደራል ፖሊስ እና ደህንነት ተቋማት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

## ክፍል ሁለት

## ክልከላና ገደብ ስለተጣለባቸው ምርቶች

### ፬. ክልከላ እና ገደብ ስለመጣል

፩/ አስተዳደሩ ክልከላ እና ገደብ የሚጣልባቸው ምርቶችን ከብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይለያል፤ በመመሪያ ያወጣል፡፡

፪/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት በመመሪያ ክልከላ ወይም ገደብ የተጣለባቸውን ምርቶች ዝርዝር በየዓመቱ ከቴክኖሎጂ እድገትና ተለዋዋጭነት አንፃር ማሻሻያ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፫/ አስተዳደሩ በኢንፎርሜሽን ደህንነት ላይ ስጋት ወይም አደጋ የሚፈጥር አዲስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርት ወደ ሀገር በሚገባበት፣ ከሀገር በሚወጣበት ወይም በሀገር ውስጥ በማንኛውም መልኩ ጥቅም ላይ በሚውልበት ወቅት ተጨማሪ ክልከላ ወይም ገደብ ሊጥል ይችላል፡፡

11/ **“Person”** means any natural or juridical person;

12/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

### 3. Scope of Application

1/ The provisions of this Proclamation shall apply to any person engaged in the importation, exportation, manufacturing, creating, sale, exchange, possession, trafficking, promotion, use, or facilitating the use of products.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, this Proclamation shall not apply to the Ethiopian National Defense Forces and Federal Police Security Institutions.

## PART TWO

## PROHIBITED AND RESTRICTED PRODUCTS

### 4. Imposition of Prohibition and Restriction

1/ The Administration shall identify and issue Directive concerning prohibited and restricted products in collaboration with the National Intelligence and Security Service and other relevant entities.

2/ The Administration shall annually revise the list of products that are prohibited or restricted through Directive in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

3/ The Administration may impose additional prohibitions or restrictions on the import, export, or local utilization of a new product that poses a threat to information security.

፬/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ክልከላ ወይም ገደብ የሚደረግባቸውን ምርቶች ዝርዝር በዌብ ሳይት እና በተለያዩ አማራጮች ለህዝብ ተደራሽ ያደርጋል።

## ፭. <u>ስለተከለከሉ ተግባራት</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፬ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የተከለከሉ ምርቶችን በመጠቀም ማንኛውንም ቁጥጥር የሚደረግበትን ተግባር ማከናወን የተከለከለ ነው።

፪/ የፀና ደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖር በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፬ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ገደብ የተደረገበትን ምርት በመጠቀም ማንኛውንም ቁጥጥር የሚደረግበትን ተግባር ማከናወን የተከለከለ ነው።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የተደነገገው ክልከላ ቢኖርም፤ ክልከላ የተደረገበትን ምርት ለትምህርት ወይም ለጥናትና ምርምር ዓላማ ወደ ሀገር እንዲገባ፣ ከሀገር እንዲወጣ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውል አስተዳደሩ መመሪያ በማውጣትና የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ሊፈቅድ ይችላል።

## ፮. <u>ስለደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ</u>

፩/ አስተዳደሩ ገደብ የተደረገበትን ምርት በመጠቀም ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

፪/ አስተዳደሩ የሚከተሉትን የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ዓይነቶች ይሰጣል፡-

ሀ) ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል ቅድመ ፈቃድ፤

ለ) ወደ ሀገር ለገቡ ምርቶች የማስለቀቂያ፤

ሐ) ምርቶች ወደ ውጪ የመላኪያ፤ ወይም

መ) ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለማምረት፣ ለመሸጥ፣ እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ፈቃድ፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተጠቀሱትን የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ዓይነቶች ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻና የአቀራረብ ሥርዓት፣ ስለማመልከቻ የማቅረቢያ ጊዜ፣ በማመልከቻ ላይ ምላሽ ስለሚሰጥበት፣ ቅሬታ ስለሚቀርብበት እና ሌሎች አግባብነት

4/ The Administration shall make available to the public the list of products that are prohibited or restricted in accordance with Sub-Article (1) of this Article, through its website and other options.

## 5. <u>Prohibited Activities</u>

1/ Performing any regulated activities using prohibited products as per Article 4, Sub-Article (1) of this Proclamation is prohibited.

2/ Performing any regulated activities using restricted products as per Article 4, Sub-Article (1) of this Proclamation without a valid security clearance permit is prohibited.

3/ Notwithstanding the prohibition provided under Sub-Article (1) of this Article, the Administration by enacting a Directive and setting up a control mechanism may issue a permit for the importation, exportation, and utilization of prohibited products for education, or research and development purposes.

## 6. <u>Security Clearance Permit</u>

1/ The Administration will issue a security clearance permit, to carry out regulated activities using restricted products.

2/ The Administration issues the following types of security clearance permits:

a) product pre-import permit;

b) product Import permit;

c) product export permit; or

d) product manufacturing, sale, and other permits to conduct regulated activity.

3/ The Administration shall issue Directives regarding the permit application process, application period, response to the application, grievance mechanism and other relevant issues for obtaining security clearance permits stipulated under Sub-Article (2) of this Article.

ያላቸው ጉዳዮችን አስመልክቶ አስተዳደሩ መመሪያ ያወጣል።

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሠረት የሚሰጠው የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ብሔራዊ ደህንነት ከማስጠበቅ እና የቴክኖሎጂዎችን የቴክኒክ ደረጃና ብቃት ከማረጋገጥ አንፃር የሚሰጡትን ፈቃድ እና ቁጥጥር አያስቀርም።

**፯. <u>የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚሰጥባቸው ዋና መስፈርቶች</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፮ መሠረት የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) የነዋሪነት መታወቂያ፣ ዲጂታል መታወቂያ፤ ፓስፖርት ወይም የሕግ ሰውነት ማረጋገጫ ሰነድ፤

ለ) አመልካች የውጭ ሀገር ዜጋ ከሆነ የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የሥራ ፈቃድ ወይም የኢትዮጵያ ቪዛ ሲያቀርብ፤

ሐ) ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በፍርድ ወይም በሕግ ችሎታውን ያላጣ መሆን፤

መ) ቋሚ አድራሻ ያለው መሆን፤እንዲሁም

ሠ) ፈቃድ እንደሚሰጥበት የቴክኖሎጂ ምርት ዓይነት ሌሎች አስተዳደሩ በመመሪያ የሚያወጣቸው ቴክኒካል መስፈርቶችን።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተቀመጡ መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ሲሟሉና የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ሲያገኝ አስተዳደሩ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል።

**፰. <u>የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ይዘት</u>**

የምርቶች የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፡-

፩/ ፈቃድ የተሰጠውን ሰው ሙሉ ስም፣ ፎቶ፣ አድራሻ፣

፪/ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂውን ዓይነት፣ ስሪት ሀገር፣ ሞዴል፣ መለያ ቁጥር፣ የምርት ዓመት፣

፫/ ፈቃድ የተሰጠበትን ዓላማ፤

4/ The security clearance permits issued in accordance with Sub-Article (1) and (2) of this Article do not affect the licensing and supervision mechanism put in place by other relevant entities for national security and verifying technical standards and competencies of technologies.

**7. <u>General Requirements for Security Clearance Permits</u>**

1/ A person applying for a security clearance permit in accordance with the provisions of Article 6 of this Proclamation shall meet the following requirements:

a) Renewed Identity Card, Digital ID, Passport, or Legal personality document;

b) when the applicant is a foreign national residence permit, work permit, or valid Ethiopian visa;

c) be not legally or by court decision incapable fully or partially;

d) permanent address; and

e) other technical requirements specified by the Administration that are related to the product to be permitted.

2/ The Administration shall issue a security clearance permit when the requirements set out under Sub-Article (1) of this Article are fully met and the application is accepted.

**8. <u>Content of Security Clearance Permit</u>**

product security clearance permit should contain the following information:

1/ The full name, photo, and address of the person with a permit;

2/ Type of the product, country of origin, model, serial number, production year;

3/ The purpose of the permit;

፬/ ፈቃድ የሰጠው የአስተዳደሩ ኃላፊ ስም፣ ፊርማ፣ ማህተም፤

፭/ ፈቃዱ የተሰጠበትንና የሚያበቃበትን ቀንና ዓመት ምህረት፤ እና

፮/ ሌሎች አስተዳደሩ እንደ ምርቱ ዓይነትና ልዩ ባህሪ በመመሪያ የሚለያቸው ይዘቶችን።

## ፱. ፈቃድ ስለሚታደስበት ሁኔታ

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው አስተዳደሩ በሚዘረጋው ሥርዓት እንደአስፈላጊነቱ በየዓመቱ የፈቃድ እድሳት ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪/ አስተዳደሩ የቀረበለትን የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ጥያቄ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስፈላጊ መስፈርቶች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ፈቃዱን ያድሳል፤

## ፲. የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታ

በዚህ አዋጅ መሠረት የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

፩/ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠበትን ምርት ለተፈቀደለት ዓላማ እና ወሰን ብቻ የመጠቀም፤

፪/ ምርቶችን አስመልክቶ የተሰጠውን ፈቃድ ወይም ፈቃድ ያገኘበትን ምርት ለሦስተኛ ወገን በማናቸውም መልኩ አስተዳደሩን ሳያሳውቅና ፈቃድ ሳያገኝ ያለማስተላለፍ፤ ያለማዋስ፣ እንዲጠቀምበት ያለማድረግ እና በሌላ ሰው እጅ እንዳይገባ የማድረግ፤

፫/ የተሰጠውን ፈቃድ ምርቱን በሚይዝበትና በሚጠቀምበት ወቅት የመያዝ፤

፬/ ለፈቃዱ መሰጠት አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች ላይ ለውጥ ሲኖር ለአስተዳደሩ ወዲያውኑ የማሳወቅ፤

፭/ ፈቃድ የተወሰደበት ምርት ሲበላሽ፣ ሲጠፋ፣ ሲሰረቅ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ከቁጥጥሩ ውጭ መሆኑን እንዳወቀ በ፰ ሰዓት ውስጥ ለአስተዳደሩ የማሳወቅ፤

4/ Name, Signature, and a Stamp of the Authorized Head of the Administration;

5/ The issuance and expiration year and date of the permit; and

6/ other contents specified by the Administrative Directives, based on the type and characteristics of the product.

## 9. Conditions for Renewal of Permit

1/ Any person granted a security clearance permit in accordance with this Proclamation, as it deems necessary shall renew his permit annually as per the procedure tobe set by the Administration;

2/ The Administration within the schedule specified in the Directive shall renew the security clearance permit upon verifying requirements have been met.

## 10. Obligation of a Person Issued with a Security Clearance Permit

Any person who has been granted a security clearance permit as per this Proclamation shall have the following obligations:

1/ Use the permitted product only for its intended purpose and limit;

2/ Not to transfer, lend, make use, or transfer custody of the security clearance permit or permitted product to a third party without prior notice and permit of the Administration;

3/ To hold the security clearance permit while handling and using the product;

4/ Immediately notify the Administration, if there is a change in any of the requirements necessary for the issuance of the permit.

5/ Notify the Administration within 8 hours after recognizing the permitted product is damaged, lost, stolen, or in any way out of its control;

፮/ አስተዳደሩ የቁጥጥር ኃላፊነቱን በሚወጣበት ወቅት የሚጠይቃቸውን አስፈላጊ መረጃዎች የማቅረብና ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ የመስጠት፤

፯/ ይህን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ ሌሎች ግዴታዎችን ማክበር፡፡

## ፲፩. የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ስለማገድ፤

አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፪ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ጥርጣሬ በሚኖርበት ወቅት ጉዳዩ እስኪጣራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ምርቱን እና የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃዱ እንዲታገድ፣ ምርቱ በአስተዳደሩ እጅ እንዲቆይ ወይም ሌላ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ እርምጃ እንዲወሰድ ሊወስን ይችላል፤

## ፲፪. የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ስለመሰረዝ

፩/ የምርቶች የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊሰረዝ ይችላል፡-

ሀ) ፈቃዱን ለማግኘት የቀረቡ መረጃዎች ሀሰተኛ ሆነው ሲገኙ፤

ለ) የተሰጠው ፈቃድ ከተሰጠበት ዓላማና ወሰን ውጪ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው ይህን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ስለመጣሱ ሲረጋገጥ፤

መ) የተሰጠው ፈቃድ የጊዜ ገደብ ሲያበቃና ሳይታደስ ሲቀር፤

ሠ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲሞት ወይም በሕግ ወይም በፍርድ ችሎታውን ሲያጣ፤

ረ) ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ሲፈርስ ወይም ሲዘጋ፤

ሰ) ፈቃዱን ለማግኘት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች ውስጥ አንዱ ሲጓደል፤

ሸ) ፈቃድ የተሰጠበት ምርት በተለያዩ ምክንያቶች ሲጠፋ፣ ሲበላሽ፣ ሲወድም በመበላሸቱ ምክንያት ከጥቅም ውጪ ሲሆን ወይም በተለያየ ምክንያት ከባለቤቱ ቁጥጥር ውጪ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

6/ To provide the necessary information requested by the Administration while fulfilling its regulatory responsibilities and to provide explanations it may require; and

7/ To comply with this Proclamation and other obligations set out in the Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation;

## 11. Suspension of permit

In case of doubt as to the exitance of any of the circumstances set out in Article 12 Sub-Article (1) of this Proclamation, if it is deemed necessary to investigate the matter, the Administration may decide to suspend the product and security clearance permit; to take the custody of the product; or to take other technology-based action;

## 12. Revocation of Security Clearance Permit

1/ security clearance permit may be revoked when:

a) the documents presented to acquire the permit are found to be forged;

b) it is verified that the permit is being used beyond the intended purpose and limit;

c) the permit holder violated this Proclamation or Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation;

d) the permit expires and is not renewed;

e) the permit holder dies or loses his capacity through legal or judicial interdiction;

f) the permit holder organization dissolves or ceases to exist;

g) one of the requirements for obtaining the permit is missing:

h) the permitted product is lost, damaged, destroyed, being out of use due to its damage or out of the control of the permit holder for various reasons;

ቀ) ባለፈቃዱ የተሰጠውን ፈቃድ በራሱ ፍላጎት ሲመልስ፤ ወይም

በ) ሌሎች አስተዳደሩ በመመሪያ የሚለያቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ።

፪/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃዱን ይሰርዛል፤ ምርቱም እንደ አግባብነቱ አስተዳደሩ በመመሪያ በሚዘረጋው አሰራር መሠረት ሊወረስ ይችላል።

## ፲፫. ክፍያ ስለመሰብሰብ

አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚፀድቅ ደንብ መሠረት ክፍያዎችን ይሰበስባል።

## ክፍል ሶስት

## የምርቶች ቁጥጥር ሥርዓት

## ፲፬. የቁጥጥር አግባብ

አስተዳደሩ የሚከተሉትን ሥርዓቶች በመዘርጋት በምርቶች ላይ ቁጥጥር ያደርጋል፦

፩/ ተጋላጭነት ባለባቸው የሃገሪቱ መግቢያና መውጫ በሮች ላይ በሚገኙ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ኬላዎች ላይ ተገቢውን ስታንዳርድ የተከተለ የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ይቆጣጠራል፤

፪/ የተቆጣጣሪ ባለሙያዎችን የፍተሻ አቅም የሚገነቡ እና ፍተሻ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች በመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች እንዲሟሉ ይደረጋል፤

፫/ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የቴክኖሎጂ ምርቶች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የኦዲት እና ግምገማ ስራ ይሰራል፤

፬/ በሀገሪቱ የሚገኙ የደህንነት ማረጋጫ ፈቃድ የተሰጣቸውን የምርቶች ዝርዝር መረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የመረጃ ቋት ያደራጃል፤

፭/ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ፣ ከሀገር የሚወጡ እና በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ምርቶችን ለመቆጣጠር የሚያስችል የቴክኖሎጂ አማራጮችን ይተገብራል፤

i) the permit holder returns the permit at his discretion; or

j) When other conditions identified by the Administration are met.

2/ When the conditions specified under Sub-Article (1) of this Article are confirmed, the Administration will revoke the permit and may confiscate the product in accordance with the procedure to be specified through Directive

## 13. Collection of Fees

The Administration shall collect fees for the services provided under this Proclamation in accordance with the Regulation to be issued by the Council of Ministers.

## PART THREE
## PRODUCTS CONTROL MECHANISMS

## 14. Control Mechanism

The Administration will control products by deploying the following methods:

1/ Setup standardize control mechanisms and control products at vulnerable entry and exit customs checkpoints of the country;

2/ ensure modern technologies required for the capacity building of inspectors and inspection of products at customs checkpoints are fulfilled;

3/ Performs timely Audit and Evaluation work on products imported into the country through security clearance permits;

4/ establish system to organize a database of permitted products within the country;

5/ implement technological platforms to control the import, export, and use of products;

፮/ የተከለከሉና ገደብ የተጣለባቸው ምርቶች ወደ ሀገር እንዳይገቡ እና ከሀገር እንዳይወጡ እና በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል

፯/ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ላይ ስጋት የሚፈጥሩ ሁኔታዎች መኖራቸው ሲታመን ወደ ሀገር በሚገቡና ከሀገር በሚወጡ የምርቶች ይዘት ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

## ፲፭. ተቆጣጣሪን ስለመሰየም

፩/ አስተዳደሩ ክልከላ እና ገደብ የተጣለባቸውን ምርቶች የሚቆጣጠሩ ባለሙያዎችን ይሰይማል፤ ኃላፊነታቸውን የሚገልፅ መታወቂያ ይሰጣል፡፡

፪/ አስተዳደሩ ተቆጣጣሪ ባለሙያዎችን ለመሰየም የሚያስችሉ መስፈርቶችን፣ የደህንነት ማጣሪያ ዘዴዎችን እና የሙያ ሥነ-ምግባር መርሆዎችን በመመሪያ ያወጣል፡፡

## ፲፮. የተቆጣጣሪዎች ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፭ መሠረት በአስተዳደሩ የተሰየመዉ ተቆጣጣሪ ባለሙያ የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖረዋል፡-

፩/ በሀገር መግቢያና መውጫ በሮች በምርቶች ላይ ቁጥጥር የማድረግ፤

፪/ ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተከትለው በሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎች የተደነገጉ ግዴታዎች ትግበራን የመከታተልና የመቆጣጠር፤

፫/ ምርት በሕገ ወጥ መንገድ በማንኛውም ቦታ ስለመያዙ ወይም ጥቅም ላይ ስለመዋሉ ምክንያታዊ ጥርጣሬ በሚኖርበት ወቅት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከሚመለከታቸው የመንግስት የፀጥታ አካላት ጋር በመተባበር በቦታው በመገኘት ፍተሻና ምርመራ የማድረግ፤

፬/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም የተረጋገጠ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ላይ አደጋ የሚጥል ሁኔታ ሲፈጠር እና የፍርድ ቤት ትዕዛዝ እስኪወጣ ምርቱ ወይም አስፈላጊ መረጃዎች ሊጠፉ፣ ሊበላሹ፣ ወይም ሊሸሸጉ

6/ collaborate with the relevant entities' security and law enforcement agencies to prevent the importation, export, and local utilization of prohibited and restricted products; the details shall be issued by Directive.

7/ in collaboration with stakeholders control the content of information communication technologies entering and leaving the country, whenever a circumstance arises that threatens information security.

## 15. Designation of Inspector

1/ The Administration shall designate professionals who inspect prohibited and restricted products; and provide them with identification stating their responsibilities.

2/ The Administration shall issue a Directive for designating inspectors, security screening methods, requirements and ethical code of conduct.

## 16. Duties and Responsibilities of Inspectors

The Inspector appointed by the Administration in accordance with Article 15 of this Proclamation shall have the following duties and responsibilities:

1/ inspect the products at the import and export check points;

2/ monitor and supervise the enforcement of the obligations provided in this Proclamation and the Regulations and Directives issued in accordance with this Proclamation;

3/ in collaboration with relevant government law enforcement agencies, search and investigate any location with court order whenever there is reasonable suspicion that product has been seized or used illegally;

4/ notwithstanding the provisions of Sub-Article (3) of this Article, to search and investigate at any location without a court order, whenever there is an imminent information security risk and

እንደሚችሉ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖር ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማንኛውም ቦታ የመግባት እና የመፈተሽ ፤ ይህ በተደረገ በ፵፰ ሰዓት ውስጥ በአቅራቢያው ለሚገኝ ፍርድ ቤት የማሳወቅ፤

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) እና (፫) መሠረት በሚደረግ ክትትልና ምርመራ የሚገኙ ሕገ ወጥ ምርቶችን የመያዝ፣ የተገኙባቸውን ቦታዎች የማሸግ፤ መረጃዎችን የመሰብሰብ፤

፮/ ምርቶችን ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ የተከለከሉ፤ ገደብ የተጣለባቸውን ምርቶች ስለመያዙ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖር ማንኛውንም ማጓጓዣ አግባብነት ካላቸው የፀጥታ አካላት ጋር በመተባበር የማስቆም፣ የመፈተሽ እና ምርቱን የመያዝ፤

፯/ የቁጥጥር ተግባሩን ካከናወነ በኋላ ወቅታዊ ሪፖርት ለአስተዳደሩ የማቅረብ።

reasonable suspicion the product or necessary evidence might be lost, damaged, or concealed before attaining court order; to notify the incident to the nearest court within 48 hours of the occurrence;

5/ seize, seal, and collect information on any illegal products acquired through search and investigation in accordance with Sub-Articles (2) and (3) of this Article;

6/ in collaboration with relevant law enforcement agencies stop, inspect, and seize any vehicle, whenever there is a reasonable suspicion of illegal possession of a restricted and prohibited product;

7/ to provide an up-to-date report to the Administration after performing the inspection function.

## ፲፯. <u>የተቆጣጣሪዉ ግዴታ</u>

ማንኛውም ተቆጣጣሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

፩/ ቁጥጥር በሚያደርግበት ወቅት ማንነቱን የሚገልፅ መታወቂያ የመያዝና የማሳየት፤

፪/ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር ወሰን ብቻ ኃላፊነቱን የመወጣት፤

፫/ በትጋት፣ በታማኝነት፣ እና በጥንቃቄ ሥራውን የመፈፀም፤

፬/ በቁጥጥር ወቅት የሚያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ወይም ሰነድ በሚስጥር የመጠበቅ፡፡

## 17. <u>The Obligation of the Inspector</u>

Every Inspector has the following obligations:

1/ hold and show his identification during inspection;

2/ to fulfill his responsibilities only within the scope of its powers and functions;

3/ perform his activity diligently, faithfully, and carefully;

4/ keep the confidentiality of any information or documents obtained as a result of the inspection.

## ፲፰. <u>ስለመያዝና መውረስ</u>

፩/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ መሠረት የተከለከሉ እና ገደብ የተጣለባቸው ምርቶች በሕገ ወጥ መንገድ ጥቅም ላይ ውለው ሲይዝ ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በመተባበር ምርቶቹን እንዲወረሱ ያደርጋል፤

፪/ አስተዳደሩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የተወረሱ ምርቶች የሚቀመጡበትን፣ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ወይም የሚወገዱበትን ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል።

## 18. <u>Seizer and Forefeiture</u>

1/ When the Administration seizes prohibited and restricted products being used illegally, it will forfeit the products in cooperation with the Customs Commission;

2/ In collaboration relevant body the Administration shall establish a procedure for storing, using, or disposing of confiscated products in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

## ፲፱. <u>የወንጀል ተጠያቂነት</u>

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) የተከለከሉ ተግባራትን የፈፀመ እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር ሃምሳ ሺ እስከ መቶ ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀው የወንጀል ድርጊት፡-

ሀ) በቸልተኛነት የተፈፀመ ከሆነ እና በሀገርና በዜጎች ደህንነት ላይ ጉዳት ካላደረሰ፤ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና እስከ ብር ሃምሳ ሺህ የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ለ) ብዛት ባላቸው ምርቶች ወይም በተደራጀ መልኩ የተፈፀመ እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር ሁለት መቶ ሺህ እስከ አምስት መቶ ሺህ የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲ እና አንቀፅ ፲፯ የተደነገጉ ግዴታዎችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና ከብር አምስት ሺህ እስከ ሃምሳ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## ፳. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው የአስተዳደሩ ተቆጣጣሪ ኃላፊነቱን ሲወጣ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ፳፩. <u>የቅሬታና አቤቱታ አፈታት ሥርዓት</u>

፩/ አስተዳደሩ ከዚህ አዋጅ አፈፃፀም ጋር ተያይዞው የሚነሱ ቅሬታዎችን የሚያስተናግድ ክፍል ያቋቁማል እና የቅሬታ አቀራረብና አፈታት መመሪያ ያወጣል፡፡

## 19. <u>Criminal Liability</u>

1/ Any person who commits any of the acts prohibited under Article 5 Sub-Articles (1) and (2) of this Proclamation shall be punished by rigorous imprisonment from three years to five years and a fine from Fifty Thousand to One Hundred Thousand Birr.

2/ Where the crime described under Sub-Article (1) of this Article:

a) is committed negligently and does not harm the security of the country and its citizens; shall be punished by simple imprisonment not exceeding three years and a fine of up to Fifty Thousand Birr;

b) is committed with large quantity of products or in an organized manner, shall be punished with rigorous imprisonment from five years to ten years, and a fine from Two Hundred Thousand to Five Hundred Thousand Birr.

3/ Any person who contravenes Article 10 and Article 17 of this Proclamation shall be punished with simple imprisonment from one to three years, and a fine from Five Thousand to Fifty Thousand Birr.

## <u>PART FOUR</u>
## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

## 20. <u>Duty to Cooperate</u>

Every person shall have the duty to cooperate with the Administration Inspector while carrying out his responsibilities.

## 21. <u>Grievance and Complaint Redressal</u>

1/ The Administration shall establish a complaint handling department and grievance and complaint redressal Directive to deal with complaints related to the implementation of this Proclamation.

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትለው በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በተላለፈበት ውሳኔ ላይ ካልተስማማ ቅሬታውን ለአስተዳደሩ የማቅረብ መብት አለው፡፡

፫/ በአስተዳደሩ የቅሬታና አቤቱታ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ አካል ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

**፳፪. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

ይህን አዋጅ ተከትሎ ክልከላ ወይም ገደብ የተደረገበትን ምርት የያዘ ማንኛውም ሰው ይህ አዋጅ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ ገደብ ለተደረገባቸው ምርቶች የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ማግኘት ወይም ክልከላ የተደረገባቸውን ምርቶች ለአስተዳደሩ ማስረከብ ይኖርበታል።

**፳፫. <u>ተፈፃሚ ስለማይሆኑ ሕጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፬. <u>ደንብና መመሪያ ስለማውጣት</u>**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፤

፪/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅና በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል።

**፳፭. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

2/ Any person who is aggrieved with the decision made in accordance with this Proclamation or Regulations and Directives issued for the execution of this Proclamation has the right to submit his complaint to the Administration.

3/ A person who is dissatisfied with the decisions of the Administration may file a complaint to the competent Court.

**22. <u>Transitional Provisions</u>**

Following this Proclamation, any person who has in his passion prohibited or restricted products must obtain a security clearance permit for restricted products or submit prohibited products to the Administration within a year from the date of this Proclamation enactment.

**23. <u>Inapplicable Laws</u>**

Any law or customary practice contrary to this Proclamation shall not apply to matters pertaining to this Proclamation.

**24. <u>Power to Issue Regulation and Directive</u>**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Administration shall issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation, and Regulations issued in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

**25. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa on this 6th day of March, 2024.**

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**